በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ምክንያት ከአገር እንዲወጡ ተደርገው
የነበሩ ኤርትራዊያን በኢትዮጵያ ውስጥ ያላቸውን ንብረት ማግኘትና ማልማት
እንዲችሉ የወጣውን የሚኒስትሮች ምክር ቤት መመሪያ
ለማስፈፀም የወጣ የአፈፃፀም መመሪያ □□□ ***530/2013***

የኤርትራ መንግስት በከፈተብን ጦርነት ምክንያት ከአገር እንዲወጡ ተደርገው የነበሩ ኤርትራዊያን በኢትዮጵያ ውስጥ ያላቸውን ንብረት ማግኘትና ማልማት እንዲችሉ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሚኒስትሮች ምክር ቤት ግንቦት 7 ቀን 2001 ዓ.ም መመሪያ ያወጣ በመሆኑ፤

ይህንኑ መመሪያ ለመተግበር የሚያስችል ዝርዝር የአፈጻጸም መመሪያ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በመሠረያው አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 6 መሶረት ከዚህ የሚከተለው የአፈፃፀም መመሪያ ወጥቷል::

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ የአፈፃፀም መመሪያ «የኤርትራ መንግስት በከፈተብን ጦርነት ምክ:ያት ከአገር እንዲወጡ ተደርገው የነበሩ ኤርትራውያን በኢትዮጵያ ውስጥ ያላቸውን ንብረት ማግኘትና ማልማት እንዲችሉ የወጣ ዝርዝር የአፈፃፀም መመሪያ» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

2. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ የአፈፃፀም መመሪያ ግንቦት 7 ቀን 2001 ዓ.ም በወጣው የኤርትራ መንግስት በከፈተብን ጦርነት ምክንያት ከአገር እንዲወጡ ተደርገው የነበሩ ኤርትራዊያን በኢትዮጵያ ውስጥ ያላቸውን ንብረት ማግኘትና ማልማት እንዲችሉ የሚኒስትሮች ም/ቤት ባወጣው መመሪያ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል::

3. <u>ትርጓሜ</u>

1) መመሪያ ማለት:- «የኤርትራ መንግስት በከፈተብን ጦርነት ምክንያት ከአገር እንዲወጡ ተደርገው የነበሩ ኤርትራውያን በኢትዮጵያ ውስጥ ያላቸውን ንብረት ማግኘትና ማልማት እንዲችሉ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ግንቦት 7 ቀን 2001 ዓ.ም ያወጣው መመሪያ» ማለት ነው::

2) የአፈፃፀም መመሪያ ማለት፡- «የሚኒስትሮች ምክር ቤት ያወጣውን መመሪያ ለማስፈፀም የወጣ የአፈፃፀም መመሪያ» ነው

3) "አብይ ኮሚቴ" ማለት፡- በመመሪያው አንቀጽ 8 መሰረት መመሪያውን ለማስፈጸም የተቋቋመ ኮሚቴ ማለት ነው፡፡

4) "ንዑስ ኮሚቴ" ማለት፡- በመመሪያው አንቀጽ 9 (6) መሠረት በአብይ ኮሚቴው የተቋቋመ ኮሚቴ ነው፡፡

4. <u>አብይ ኮሚቴው የሚያከናውናቸው ተግባራት</u>

በመመሪያው አንቀፅ 9 የሰፈረው እንደተጠበቀ ሆኖ ኮሚቴው ከዚህ የሚከተሉትን ተግባራትን ያከናውናል፤

1. በመመሪያው አፈፃፀም ሂደት የሚከሰቱ የአፈፃፀም ችግሮችን በሚመለከት በየጊዜው በንዑስ ኮሚቴው የሚቀርብለትን ሃሳብ መነሻ በማድረግ ከሚመለከታቸው ወገኖች ጋር የጋራ ውይይት በማድረግ የመፍትሔ አቅጣጫዎችን ይወስናል፡፡ የተከሰቱ ችግሮችና የአፈፃፀም ማነቆዎች መፈታታቸውን ይከታተላል፡፡

2. በንዑስ ኮሚቴው የሚቀርብለትን ወርሃዊ ሪፖርት እና በየ 15 ቀናት የሚቀርብለትን የእንቅስቃሴ (progress) ሪፖርቶችና የውሳኔ ሀሳብ መርምሮ ያፀድቃል፡፡

3. ውስብስብና አከራካሪ እንዲሁም ከብሔራዊ ፀጥታና ደህንነት ጋር ንኪኪ ያላቸውን ንብረት ነክ ጉዳዮች እየመረመረ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

4. የመንግሥት ኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት እና ሌሎች አግባብነት ያላቸውን አካላት በማሳተፍ በየጊዜው ስለመመሪያው ዓላማ ግንዛቤ ማስጨበጫ የቅስቀሳና ሌሎች የሕዝብ ግንኙነት ሥራዎች ስለሚመቻቹበት ሁኔታ መመሪያ ይሰጣል፡፡ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፡፡

5. በመመሪያው እና በዚህ የአፈፃፀም መመሪያ የተመለከቱት ተግባራት ከሚመለከታቸው የፌዴራልና ክልል አካላት ጋር ግንኙነት በማድረግ በጋራ ማከናወን የሚቻልበትን ሁኔታ ማመቻቸቱን ያረጋግጣል፤ የመመሪያውንም አፈፃፀም በየጊዜው ይከታተላል፡፡

6. በመመሪያው አንቀጽ 3 መሠረት ተሟልተው የሚቀርቡ የንብረት ክስተዳደር ጥያቄዎችን በመመርመር ውሳኔ ይሰጣል፡፡

7. ከአገር እንዲወጡ የተደረጉ ኤርትራዊያን በባንክ የተቀመጠ ገንዘባቸውን በሚመለከት ጥያቄዎችንና ማስረጃዎችን በመመርመር በመመሪያው አንቀጽ 4 መሠረት ማውጣትና ማንቀሳቀስ እንዲችሉ ይወስናል፡፡

8. በመመሪያው አንቀጽ 5 መሠረት የሚቀርቡ የኢንቨስትመንት ሥራ ጥያቄዎች/በኢንቨስትመንት አዋጅ እና ተያያዥ ህጐች መሰረት በኤጀንሲው በኩል እንዲስተናገዱ ያደርጋል፡፡

9. በሌላ ሕግ አግባብነት ላለው አካል የተሰጠው ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ የቪዛና የመኖሪያ ፈቃድ ጥያቄ ሲቀርብለት የጥያቄውን አግባብነት መርምሮ በመመሪያው አንቀጽ 6 መሠረት ፈቃድ ይሰጣል፡፡

10. ስለመመሪያው ዓላማ እና አፈፃፀም በየጊዜው ለአስፈፃሚ አካላት የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮችን እንዲዘጋጁ ያደርጋል፣

11. በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገሮች በመገናኛ ብዙሀን እና የተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎች በመጠቀም የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነቶችን ለማጠናከር የሚያስችሉ ተግባራት በየጊዜው እንዲሰሩ ያደርጋል፡፡

12. አብይ ኮሚቴው ከዚህ በላይ በአንቀፅ 3 ከተመለከቱት ውስብስብና አከራካሪ እንዲሁም ከብሔራዊ ፀጥታና ደህንነት ጋር ተያያዥነት ካላቸው ንብረት ነክ ጉዳዮች በስተቀር በዚህ አንቀፅ ሥር የተዘረዘሩትን ተግባራት እንዲያከናውን ለንቡስ ኮሚቴው በውክልና ማስተላለፍ ይችላል፡፡

13. መሠረታዊያውን ለማስፈጸም የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

5. <u>ስለ ኮሚቴው አወቃቀር</u>

1. በመመሪያው አንቀጽ 8 መሠረት የተቋቋመው አብይ ኮሚቴ 4 አባላት ይኖሩታል፡፡ የኮሚቴው አባላትም ዝርዝር እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

ሀ) የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሚኒስትር፣ ወይም የሚወክለው ተወካይ የኮሚቴው ሠብሳቢ፣

ለ) የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሚኒስትር፣ ወይም የሚወክለው ተወካይ የኮሚቴው አባል፣

ሐ) የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር፣ ወይም የሚወክለው ተወካይ የኮሚቴው አባል ሆነ፣

መ) የፌደራል ፖሊስ ዋና ዳይሬክተር፣ ወይም የሚወክል ተወካይ የኮሚቴው አባል ናቸው፡፡

2. ኮሚቴው በህግ የተሰጡትን ተግባራት ለማከናወን የሚስችለውን የሰው ኃይል አግባብነት ካላቸው የመንግስት መስሪያ ቤቶች በጊዜያዊ ዝውውር ወይም በቅጥር ያሟላል፡፡

3. ኮሚቴው በዚህ የአፈጻጸም መመሪያ አንቀጽ 6 የተዘረዘሩትን ተግባራት የሚያከናውን ንዑስ ኮሚቴ ያቋቁማል፡፡ የንዑስ ኮሚቴ ሰብሳቢ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የውጭ ጉዳይ ሚ/ር ተወካይ ይሆናል፡፡

4. ንዑስ ኮሚቴው ስራውን የሚያከናውንበት ጊዜያዊ ጽ/ቤት ይኖረዋል፡፡

6. ስለቅሬታ አቀራረብ ሥርዓት

1. በመመሪያው በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ አብይ ኮሚቴው ወይም በንዑስ ኮሚቴው ከሚሰጣቸው ውሳኔዎች አፈፃፀም ጋር በተያያዘ በተከሰተ ችግር ቅር የተሰኘ ወገን በፍትሀብሔር ህጉ በተደነገገው መሰረት ከአቅም በላይ ካልሆነ በስተቀር ቅሬታውን በ60 ቀናት ውስጥ ለአብይ ኮሚቴው ማቅረብ አለበት፡፡

2. በፍርድ ቤት በመታየት ላይ ባሉ ወይም የመጨረሻ ውሳኔ በተሰጠባቸው ወይም በዕዳ ምክንያት በተያዙ ወይም በተሸጡ ወይም አከራካሪ ይዘት ኖሯቸው ለፍርድ ቤት መቅረብ በሚገባቸው ጉዳዮች ላይ ቅሬታ ማቅረብ አይቻልም፡፡

3. ቅሬታ የሚቀርበው የግጭበርበር ወይም አጠራጣሪ ሁኔታ የሚታይባቸው፣ ወይም ጋገባኛል ባዩ ወይም ወኪሉ ወይም ውሳኔ ፈፃሚ አካል ያልተማመኑባቸው አከራካሪ ያልሆኑና ወደ ፍ/ቤት መቅረብ የማያስፈልጋቸው ጉዳዮች ብቻ አስመልክቶ ይሆናል፡፡

4. አብይ ኮሚቴው የቀረበለትን ቅሬታ መርምሮ በ1 ወር ጊዜ ውስጥ ተገቢ መስሎ የታየውን ውሳኔ ይሰጣል፡፡

ንዑስ ኮሚቴው የሚያከናውናቸው ተግባራት

7. የንዑስ ኮሚቴው ተግባራት

በመመሪያው አንቀጽ 9 (6) እና በዚህ የአፈፃፀም መመሪያ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት የሚቋቋመው ንዑስ ኮሚቴ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል፣

1. የንዑስ ኮሚቴው ተጠሪነት ለአብይ ኮሚቴው ይሆናል፡፡ በመመሪያው አንቀጽ 8 ከተዘረዘሩት መ/ቤቶች የተወከሉ 4 አባላት ይኖሩታል፡፡

2. በዚህ መመሪያ አንቀፅ 4 ንዑስ አንቀፅ 5 መሠረት በአብይ ኮሚቴው በውክልና የሚሰጡትን ጉዳዮችን በሚመለከት የሚቀርቡ ማመልከቻዎችንና አቤቱታዎችን ይመረምራል፣ ውሳኔ ይሰጣል፣ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፣

3. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት የሚቀርቡ ማመልከቻዎች በዚህ የአፈጻጸም መመሪያ መሰረት ተሟልተው መቅረባቸውን ያጣራል፡፡

4. አመልካቾች ያቀረቡት ማመልከቻ በመመሪያውና በዚህ የአፈጻጸም መመሪያ መሰረት ተቀባይነት ያላቸው መሆን አለመሆኑን የቀረቡለትን መረጃና ማስረጃዎች በመመርመር የውሳኔ ሃሳብ አዘጋጅቶ ለአብይ ኮሚቴው ያቀርባል፡፡

5. በአብይ ኮሚቴው ወይም በንዑስ ኮሚቴው የተሰጡ ውሳኔዎችን አፈፃፀም በሚመለከት ለፅ/ቤቱ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን ተቀብሎ ይመረምራል፣ አፈፃፀማቸውን ይከታተላል፡፡

6. የንዑስ ኮሚቴውን ወርሃዊ የክንውን ሪፖርት ለአብይ ኮሚቴው ያቀርባል፣ በየ15 ቀናት የእንቅስቃሴ (progress) ሪፖርቱንና አጠቃላይ ወርሃዊ ሪፖርት ለአብይ ኮሚቴው ያቀርባል፡፡

7. ከዚህ ጋር ግንኙነት ያላቸውን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፣

8. <u>ስለ ጽ/ቤት</u>

1. በሚኒስትሮች ም/ቤት መመሪያና በዚህ የአፈፃፀም መመሪያ መሠረት የተመለከቱትን ተግባራት በተደራጀ መልክ ለመምራት የሚያስችል ጊዜያዊ ጽ/ቤት ተቋቁሟል፡፡

2. ጊዜያዊ ጽ/ቤቱ ተጠሪነት ለንዑስ ኮሚቴው ይሆናል፡፡

3. ጊዜያዊ ጽ/ቤቱ በመመሪያውና በዝርዝር የአፈፃፀም መመሪያው የተመለከቱትን ተግባራት ለማስፈፀም ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ተግባራት ያከናውናል፡፡

ሀ) የኮሚቴውን የሥራ ዕቅድና በጀት ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፣

ለ) ለጽ/ቤቱ በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት በፌዴራል የመንግሥት ሠራተኞች ሕግ አግባብ እንደአስፈላጊነቱ ለጽ/ቤቱ የሚያስፈልጉ ጊዜያዊ ሠራተኞችን ይቀጥራል፣ በጊዜያዊ ዝውውር የተሰባሰቡ ሠራተኞችን ያስተዳድራል፣

ሐ) በአመልካቾች የሚቀርቡ ማመልከቻዎችንና ማስረጃዎችን ይቀበላል፣ ይይዛል ሌሎች አግባብነት ያላቸው መረጃዎችን እና ሪኮርዶችን ይይዛል፣

በአግባቡ መያዛቸውን ያረጋግጣል፣ ለንዑስ ኮሚቴው አደራጅቶ ለውሳኔ ያቀርባል፣

መ) ማናቸውንም የአብይ ኮሚቴውንም ሆነ የንዑስ ኮሚቴውን ቃለ-ጉባኤዎች፣ ውሳኔዎች፣ የደብዳቤ ልውውጦችና አግባብነት ያላቸውን ሰነዶች ይይዛል፣ ያደራጀል፣

ሠ) አብይ ኮሚቴው ወይም እንደአግባብነቱ ንዑስ ኮሚቴው በቀረቡላቸው ጉዳዮች የሚሰጧቸውን ውሳኔዎች ለባለጉዳዮች ያሳውቃል፣

ረ) በመመሪያውና በአፈፃፀም መመሪያው የተመለከቱትን ጉዳዮች ለማስፈፀም የሚያግዙ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

ሰ) የዕ/ቤቱ ኃላፊ በአብይና በንዑስ ኮሚቴው ስብሰባ ይሳተፋል ቃለ-ጉባኤ ይይዛል፤ በውሳኔ ላይ አይሳተፍም፡፡

9. <u>በመመሪያውና በዚህ አፈፃፀም መመሪያ መሠረት ስለሚቀርቡ ማመልከቻዎችና አቤቱታዎች</u>

በመመሪያው እና በዚህ የአፈፃፀም መመሪያ መሠረት ማመልከቻ የሚያቀርብ አመልካች የሚከተሉትን መስፈርቶች አሟልቶ ማቅረብ አለበት፡፡

1. የማንነት መታወቂያ ወይም ፓስፖርት፣ ዋናውንና ፎቶ ኮፒ፣
2. በዚህ ሕግ መሠረት የተሰጠና እገልግሎቱ ያላበቃ ቪዛ ወይም ሥልጣን ካለው የኢትዮጵያ የመንግሥት አካል የተሰጡ ህጋዊ ማስረጃዎች፣
3. ከዚህ የአፈፃፀም መመሪያ ጋር በአባሪነት የተያያዘው ቅጽ የሚጠይቀውን መረጃ ያሟላና የአመልካቹ ፊርማ የስፈረበት ማመልከቻ፣ ወይም የጣት አሻራ፣
4. አመልካቹ ወኪል በሚሆንበት ጊዜ በዚህ አንቀፅ ከንዑስ አንቀጽ 1-3 ከተመለከተው በተጨማሪ ወኪሉ በኢትዮጵያ የውክልና ሕግ መሠረት የተሟላና የተረጋገጠ ሕጋዊ የውክልና ሥልጣን ማረጋገጫ ሰነድ እና ማንነቱን የሚገልጽና መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናውንና ፎቶኮፒ፣
5. አመልካቹ ወኪል በሚሆንበት ጊዜ በንዑስ 4 ከተገለፀው በተጨማሪ በትርብ ጊዜ የተነሳው መጠኑ ባለ 3 x 4 የሆነ 4 ባለቀለም ጉርድ ፎቶግራፍ፣

10. <u>የግል ንብረትን በተመለከተ የሚቀርብ ማመልከቻ ይዘት፣</u>

ማንኛውም ሕጋዊ የሆነ ንብረት አለኝ የሚልና በመመሪያው መሠረት ለማመልከት የተፈቀደለት ግለሰብ የማይንቀሳቀስና ተንቀሳቃሽ ንብረት በሚመለከት በንብረቱ ላይ

ያለውን መብት የሚያረጋግጡለት በሕግ የተፈቀዱ ማስረጃዎችን በማያያዝ ለኮሚቴው ማመልከቻ ማቅረብ ይችላል፡፡

11. <u>የማይንቀሳቀስ ንብረት ጥያቄ ማመልከቻ ይዘት፣</u>

የማይንቀሳቀስ ንብረትን በሚመለከት ጥያቄ የሚያቀርብ በመመሪያው በተፈቀደው መሠረት የተፈቀደለት ማንኛውም አመልካች በዚህ የአፈጻጸም መመሪያ አንቀጽ 9 ከተጠቀሰው በተጨማሪ የሚከተሉትን ሰነዶች ከማመልከቻው ጋር አሟልቶ ማቅረብ አለበት፡፡

1. በስራ ላይ ባሉ አግባብነት ባላቸው የአገራችን ሕጐች መሠረት የፀና የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር ወይም ካርታ፣
2. በኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች የንብረት ባለቤትነት መብትን በማረጋገጥ የተሰጠ የመጨረሻ ውሳኔ፣
3. <u>በኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች</u> የተሰጠ የውርስ ወይም የስጦታ ማረጋገጫ ሰነድ፣ እና
4. ሌሎች ንዑስ ኮሚቴው እንደአስፈላጊነቱ የቀረቡለትን ንብረት ነክ ጉዳዮች ለማጣራት ያስፈልጋሉ የሚላቸውንና ሌሎች አግባብነት ያላቸው ሰነዶች፣

12. <u>የሚንቀሳቀስ ንብረት ጥያቄ ማመልከቻ ይዘት</u>

1. የሚንቀሳቀስ ንብረትን በተመለከተ የሚቀርብ ማመልከቻ በዚህ የአፈጻጸም መመሪያ አንቀጽ 9 ከተጠቀሰው በተጨማሪ የሚከተሉት ሰነዶች ጋር ተሟልቶ መቅረብ አለበት፡፡

ሀ/ ማመልከቻው የቀረበው የግል መገልገያ የተሽከርካሪ ባለቤትነትን መብትን በማስመልከት ሲሆን፣

1. አመልካቹ ከአገር እንዲወጣ ሲደረግ የታደሰ የተሽከርካሪ ባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር (ሊብሬ) እንዲሁም ንብረቱ ከዕዳ እና አገዳ ነፃ መሆኑን የሚያሰረዳ ሰነድ፣
2. ተሽከርካሪው የሚገኝበትን ትክክለኛ ቦታና አድራሻ ወይም
3. ንብረቱ በውርስ ወይም በስጦታ የተገኘ ሲሆን ውርሱ ወይም ስጦታው የተረጋገጠበት ህጋዊ ሰነድ እና ከኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች የተሰጠ የአፈጻጸም ትእዛዝ እንዲሁም ከአግድና እዳ ነፃ መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ፣
4. ሌሎች አግባብነት ያላቸው ደጋፊ ሰነዶች፣

ለ/ ማመልከቻው የቀረበው የንግድ ተሽከርካሪን የሚመለከት ሲሆን ከላይ በንዑስ አንቀጽ 1(ሀ) ከተመለከተው በተጨማሪ ተሽከርካሪው ከማንኛቸውም እዳና እገዳ ነፃ መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ ከማመልከቻው ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት፣

13. በባንክ የተቀመጠ ገንዘብ ማመልከቻ ይዘት

1. ማንኛቸውም በቁጠባ ወይም/እና በዝግ የባንክ የሂሳብ ደብተር ወይም/እና በማንኛውም መልኩ በባንክ የተቀመጠ ገንዘብ ወይም ንብረት ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ በዚህ የአፈፃፀም መመሪያ አንቀጽ 9 ከተመለከተው በተጨማሪ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን አሟልቶ መቅረብ አለበት፡፡

1. በቁጠባና በተንቀሳቃሽ የባንክ ሂሳብ የተቀመጠ ገንዘብን በተመለከተ፣

ሀ) የቁጠባ ሂሳብ ደብተር ወይም፣

ለ) ደብተሩ በማይኖርበት ጊዜ ወይም ደብተሩ እንዳያገለግል ሆኖ ቢበላሽ ወይም ቢጠፋ ይህንን የሚያስረዳ ገንዘቡ ከተቀመጠበት ባንክ በምትክነት የተሰጠ ደብተር ወይም ማስረጃ፣

2. አስቀማጩ በሕይወት የሌለ ሲሆን፣

ሀ) ሥልጣን ባለው ፍርድቤት የተሰጠ የተረጋገጠ የወራሽነት መብት ማረጋገጫ ማስረጃ፣

3. ገንዘቡ በስጦታ የተላለፈ ሲሆን፣

ሀ) ውሳኔው በኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች የተሰጠ ከሆነ የውሳኔውን ዋና እና ግልባጭ እንዲሁም የአፈጻጸም ትዕዛዝ፣ ወይም

4. በዝግ የባንክ ሂሳብ የተቀመጠ ገንዘብ ጥያቄ ሲቀርብ በዚህ የአፈፃፀም መመሪያ አንቀጽ 9 ከተመለከተው በተጨማሪ፡-

ሀ) ሕጋዊ የባንክ ሂሳብ ደብተር፣ ወይም

ለ) ንብረቱ በዕዳ ምክንያት ተሸጦ ቀሪው በዝግ የባንክ ሂሳብ የተቀመጠን ገንዘብ ለማግኘት የሚቀርብ አቤቱታ ንብረቱ በዕዳ እንዲሸጥ የታዘዘበትን ሰነድ ወይም ሰነዱን ለማግኘት የማይቻል ሲሆን ሰነዱ የሚገኝበትን ቦታ መግለጽ አለበት፡፡

5. የአክሲዮኖች ድርሻና ዲቪደንዶችን በተመለከተ የሚቀርብ ጥያቄ በዚህ የአፈፃፀም መመሪያ አንቀጽ 9 ከሰፈረው በተጨማሪ፣

ሀ) በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት የፀና የአክሲዮን ባለድርሻነት ማረጋገጫ ደብተር ወይም ሰነድ፣

ለ) አክሲዮኑ በዕዳ እና እገዳ ያልተያዘ መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ፣

ሐ) አክሲዮኑ ዋጋ ያለው እና በማንኛቸውም ምክንያት ለሦስተኛ ወገን ያልተላለፈ መሆኑን የሚያስረዳ ከአክሲዮን ማሕበሩ የተፃፈ ማስረጃ፣

መ) የአክሲዮን ባለመብትነት የተላለፈው በሕግ ሲሆን በኢትዮጵያ ፍ/ቤቶች የተሰጠ ውሳኔ ዋና እና ግልባጭ ሰነድ እና የአፈፃፀም ትዕዛዝ፣ እና

ሰ) ሌሎች ከዚህ ጋር አግባብነት ያላቸው ሌሎች ሰነዶችን ከማመልከቻው ጋር ተያይዘው መቅረብ አለባቸው።

14. በኢንቨስትመንት ሥራ ላይ ለመሰማራት የሚቀርብ ማመልከቻ ይዘት

ማንኛቸውም በኢንቨስትመንት ሥራ ላይ ለመሰማራት የሚቀርብ ማመልከቻ በዚህ የአፈፃፀም መመሪያ አንቀጽ 9 ከተመለከተው በተጨማሪ፡-

1. በአዋጅ ቁጥር 280/94 መሠረት የተደነገጉ መስፈርቶችን፣
2. በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ወይም ንግድ ባንክ ወይም እንደአስፈላጊነቱ በኮሚቴው በሚመረጥ እና በኢትዮጵያ ህግ መሰረት በኢትዮጵያ ውስጥ በተቋቋመ ባንክ የተከፈተ የባንክ ሂሳብ ደብተር እና
3. ከዚህ ጋር አግባብነት ያላቸው ሌሎች ማስረጃዎች ተሟልተው መቅረብ አለባቸው፣

15. ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

1. በዚህ መመሪያ መሰረት የሚቀርቡ ማመልከቻዎችና አቤቱታዎችን ለማስረዳት የሚቀርቡ የሰነድ ማስረጃዎች ዋና ቅጂ ሆነው በሚመለከተው ህጋዊ አካል የተረጋገጡ መሆን አለባቸው። ዋናው ሰነድ በተለያዩ ከአትም በላይ የሆኑ ምክንያቶች ማትረብ የማይቻል ሲሆን ሰነዱን ለማግኘት ያልተቻለበትን ምክንያት በማስረዳት ሰነዱ የሚገኝበትን ቦታ ማመላከት ያስፈልጋል።

2. እንደአስፈላጊነቱ ማንኛውም አመልካች ወይም የይገባኛል መብት ጠያቂ ጉዳዩ ውሳኔ ከማግኘቱ በፊት ተቃዋሚ ስለመኖሩ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ አሳውቆ ማስረጃውን ማቅርብ አለበት፡፡

3. ማንኛውም በመመሪያው መሰረት የንብረት ነክ ጉዳዮች ላይ ተመስርቶ የይገባኛል መብት ጠያቂ የሚያቀርበው አቤቱታ ተቀባይነት የሚያገኘው የፍርድ ቤት ውሳኔ ወይም ትእዛዝ ሲቀርብ ብቻ ነው፡፡

16. መሸጋገሪያ ድንጋጌ

1. ይህ የአፈጻጸም መመሪያ በማንኛውም ፍርድ ቤት በክርክር ላይ ባሉ ወይም የመጨረሻ ፍርድ ባላገኙ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

2. ይህ የአፈጻጸም መመሪያ ከዚህ ቀደም በነበሩ የአፈጻጸም መመሪያዎች መሰረት እልባት ባገኙ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

3. ማናቸውም ከዚህ የአፈጻጸም መመሪያ ጋር የሚጋጩ የአሰራር ልምዶች ወይም የአፈጻጸም መመሪያዎች በዚህ የአፈጻጸም መመሪያ በሚመለከታቸው ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

4. በዚህ የአፈፃፀም መመሪያ በአንቀፅ 16 (2) ላይ የሰፈረው ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ መመሪያ በሕገ-ወጥ መንገድ የተያዙ ወይም የተላለፉ ንብረቶችን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

17. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ የአፈፃፀም መመሪያ ከ ነሐሴ 1 ቀን 2001 ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡